www.abyssinialaw.com



11ኛ አመት ቁጥር 10
11th Year No

ባህር ዳር የካቲት 13 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar 20th, February 2006

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
## IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHHIOPIA


| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 4.70 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |


| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 38/1998 ዓ.ም | Regulation No. 38/2005 |
| የአላጥሽ ፓርክ አከላለልና አስተዳደር መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Alatish Park Demarcation and Administrative Determination, Council of Regional Government Regulation. |

ደንብ ቁጥር 38/1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአላጥሽ ፓርክ አከላለልና አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

የክልሉን ቆላማ ስርዓተ ምህዳር በሚወክል መንገድ በክልሉ ሰሜናዊ ምዕራብ አካባቢ

REGULATION NO. 38/2005

A REGULATION ISSUED BY THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT TO PROVIDE FOR THE DEMARCATION AND ADMINISTRATIVE DETERMINATION OF THE ALATISH PARK IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

Whereas, it has been found appropriate to create a favorable condition whereby the wildlife, birds and

www.abyssinialaw.com



ለሚገኙት የዱር እንስሳት፣ አዕዋፍና እፅዋት ዝርያዎች በቂ ጥበቃና እንክብካቤ በማድረግ ለመጪው ትውልድ በቅርስነት የሚተላለፉበትንና ለአካባቢው ነዋሪ ሕብረተሰብም ሆነ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከሰሀራ አካባቢ ተነስቶ በጐረቤት ሀገር በኩል ወደ ክልላችን ሊዛመት የሚችለውን የበረሃማነት መስፋፋት አደጋ ከወዲሁ በመከላከል የክልሉ ጤናማ ስርዓት-ምህዳር እንዲጠበቅ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በክልሉ የተፈጥሮ ሀብትና በተለይም በዱር እንስሳቱ ላይ ከጐረቤት ሀገሮች በኩል በየወቅቱ ድንበር አቋርጠው በሚገቡ ከብት አርቢዎችና በብዙ ሺ በሚቆጠሩ እንስሶቻቸው እንዲሁም በአካባቢው ነዋሪዎች አማካኝነት እየደረሰበት ያለው አሉታዊ ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣበትን ሁኔታ በመቀልበስ የብዝሀ ህይወት ሀብቱን ከጥፋት መታደግ በማስፈለጉ፤

የክልሉን የተፈጥሮ ሀብት ልማትና የአካባቢ ጥበቃ እንቅስቃሴ ከአጐራባች ክልሎች እንቅስቃሴ ጋር በማስተሳሰር አካባቢው ሁሉን አቀፍ እንክብካቤ የሚያገኝበትንና የዱር እንስሳቱ በተፈጥሯዊ መኖሪያቸው የሚያደርጉት ነፃ እንቅስቃሴ ከአደጋ የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለዚህም ይረዳ ዘንድ ለጊዜው ተፈላጊ መስፈርቶችን ስለማሟላቱ የተረጋገጠለትንና በቋራ ወረዳ የሚገኘውን የአላጥሽ አካባቢ በፓርክነት መሰየምና ወሰኖቹን ከልሎ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ባለቤትነት ስር የሚተዳደርበትን ህጋዊ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፤

የብሔራዊ ክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

plant species located in the north-western part of the Region are efficiently looked after, protected in a manner that represents the lowland ecosystem of the Region and passed down to the forthcoming generation as heritages and thereby contribute to the local inhabitants as well as to the national economic development;

Whereas, it has been necessary to cause the maintenance of healthy ecosystem of our Region by preventing in advance the hazards due to the expansion which desertification may possibly extend to our country via the neighboring state from around the Sahara Area;

Whereas, it is vital to protect the biodiversity resources from destruction by averting the adverse pressure being exerted and aggravated from time to time on the natural resource especially the wildlife of the Region, by the cattle-raisers and their thousands of cattle coming across the territory occasionally from the neighboring countries as well as by the local community;

Whereas, it is found appropriate to coordinate the development of natural resource and environmental protection activities of the Region with the activities of the neighboring Regions and thereby facilitate conditions wherein the locality obtains an all-out conservation and protect from danger the free movement of the wildanimals as they enjoy their natural habitat;

Whereas, it is, to assist the purpose, necessary to create a legal framework for the Alatish area situated in the Quara Woreda and for the time being confirmed to have met the essential requirements to be designated as a park as well as be administered under the management of an authorized government body, delimiting its boundaries thereof;

Now, therefore, the Council of the Amharic National

www.abyssinialaw.com



በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 96/1996 ዓ.ም አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአላጥሽ ፓርክ አከላለልና አስተዳደር መወሰኛ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 38/1998 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ፓርክ" ማለት የዱር እንስሳትና የአዕዋፍ ክምችት የተፈጥሮ መጠለያ እንዲሁም የልዩ ልዩ እጽዋት መገኛ በመሆን የታወቀውና በዚህ ደንብ መሠረት ልዩ ጥበቃ እንዲደረግለት ወሰኑ ተለይቶ የተከለለው የአላጥሽ ፓርክ ነው።
2. "ጉልት" ማለት ከድንጋይ፣ ከኮንክሪት፣ ከብረት ወይም ከሌላ ቋሚ ከሆነ ነገር ተሰርቶ በመሬት ላይ የተተከለ የወሰን መለያ ምልክት ነው።
3. "የዱር እንስሳት" ማለት ለማዳ ያልሆኑና በየብስም ሆነ በውሃ ውስጥ የሚኖሩ ልዩ ልዩ ዝርያ ያላቸው በተፈጥሮ የሚገኙ በምድር የሚሄዱና በአየር የሚበሩ እንስሳትን የሚያጠቃልል፣ የመኖሪያ፣ የመጠለያና የመራቢያ አካባቢዎችን ጭምር ያካተተና ሥነ-ሕይወታዊ ሀብትን የሚገልጽ ሃረግ ነው።

Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art 58, Sub-art. 7 of the Revised Regional Constitution and Art 24, sub-art. 1 of the Parks Development and Protection Authority Establishment and Determination of Powers and Duties Proclamation No. 96/2003, hereby issues this regulation:

## 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Alatish Park Demarcation and Administrative Determination, Council of Regional Government Regulation No38/2005."

## 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this regulation:

1. "Park" means the Alatish Park recognized as possessing the distinction of a natural habitat for wild animals and flock of birds as well as the source of various plant species and with its boundaries being identified and, demarcated, is given special care thereof, pursuant to this regulation.
2. "Post" means a landmark which is made up of stone, concrete, metal or any other fixed object.
3. "Wild life" means a phrase that accommodates a host of untamed, terrestrial and aquatic various species of animals found in nature, move on land and fly in the air, also encompassing their habitat, sanctuary and breeding areas, and is thereby an expression of diverse biological resources.

www.abyssinialaw.com



## 3. ስለፓርኩ ስያሜ፣ አከላለልና ወሰኖች

1. በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመው ፓርክ አካባቢውን መሐል ለመሐል አቋርጦ ከሚፈሰው ወንዝ መጠሪያ በመነሣት የአላጥሽ ፓርክ ተብሎ ተሰይሟል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተሰየመው ፓርክ በሰሜን ጎንደር ዞን በቋራ ወረዳ አስተዳደር የሚገኝና በጠቅላላው 266570 ሄክታር ቦታ የሚሸፍን ሆኖ በደቡብ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል፣ በሰሜን ከመሐዲድ ቀበሌ አስተዳደር፣ በምስራቅ ከባምባሆና ገለጎ ቀበሌ አስተዳደሮች እንዲሁም በምዕራብ ከሱዳን ጋር ይዋሰናል።

3. የፓርኩን አከላለልና አዋሳኝ ሥፍራዎቹን በኬክሮስ (ላቲቲዩድ) እና በኬንትሮስ (ሎንግቲዩድ) ነጥቦች ውስጥ የሚያሳየው ዝርዝር መግለጫ ከዚህ በታች ተመልክቷል።

   ሀ. ፓርኩን በምስራቅ በኩል ከሚያዋስነውና በገለጎ ቀበሌ ከሚገኘው የአልቢድ ወንዝ ላይ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አልቢድ ኮረብታ አጠገብ ከወንዙ ዳርቻ ላይ በ12 ዲግሪ 29 ደቂቃ 17.2 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 48 ደቂቃ 33.2 ሴኮንድ ምስራቅ የተፃፈውንል ጉልት ቁጥር አንድ መነሻ በማድረግ፣

   ለ. በዚያው አቅጣጫ በ12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 29.6 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 47 ደቂቃ 49.4 ሴኮንድ ምስራቅ የተፃፈውን ጉልት ቁጥር

## 3. Designation, Demarcation and Boundaries of the Park

1. The park, established pursuant to this regulation, is hereby designated as " The Alatish Park" after the name of the river that flows dividing the interior of the area by half in the middle of the locality.

2. The park so designated, pursuant to sub-art. 1 of this article, is mean to wholly cover 266570 hectares of land and located in the Quara warda Administration of the north Gonder zone, sharing borders with the Benishangul Gumuz National Regional State to the South, the Mehadid Kebele Administration to the north, Banbaho and Gelego Kebele Administrations to the east as well as the Sudan to the west.

3. The detailed description showing the demarcation of the park and its adjoining places on latitudinal and longitudinal points is indicated herebelow:

   A. Commencing at the Albid River which is found in Gelego Kebele and borders with the park to the east and turning to westerly direction near the Albid hill at the bank of the river, 12 degrees, 29 minutes, 17.2 seconds north and 35 degrees, 48 minutes, 32.2 seconds east (Post No. 1 as a starting point);

   B. Following the same direction, 12 degrees, 07 minutes, 29.6 seconds north and 35 degrees, 47 minutes, 49.4 seconds east wards (Post No. 2);

www.abyssinialaw.com



ሁለት በመከተል፣

ሐ. ከዚያም በ12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 45.5 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 47 ደቂቃ 28.3 ሴኮንድ ምስራቅ ደራሃሰን አፋፍ ጠርዝ ሾላ ውሃ ላይ እስከተፃፈው ጉልት ቁጥር ሦስት፣

መ. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የደራሃሰን ተራራን አፋፍ ለአፋፍ ተከትሎ ሂዶ እስከ ገለጎ ቀበሌ መጨረሻ አልዋሾ ተራራ ድረስ በመሄድ ከመሃዲድ ቀበሌ ከአልዋሾ ተራራ ሥር የሚነሣውን የአልዋሾን ሸለቆ ተከትሎ ሸለቆውና የአላጥሽ የበጋ የመኪና መንገድ መገናኛ ላይ በ12 ዲግሪ 15 ደቂቃ 07.3 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 44 ደቂቃ 16.5 ሴኮንድ ምስራቅ የተፃፈውን ጉልት አራት ይዞ፣

ሠ. ከዚያም ሸለቆውን በመከተል ሸለቆው ከበርሚል ወንዝ የሚገናኝበት ቦታ ላይ በ12 ዲግሪ 16 ደቂቃ 10.9 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 43 ደቂቃ 16.2 ሴኮንድ ምስራቅ እስከተፃፈው ጉልት ቁጥር አምስት ድረስ፣

ረ. ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ የበርሚል ወንዝን በመከተል በአምራኩባ ተራራ ትክክል በወንዙ ጠርዝ ላይ በ12 ዲግሪ 18 ደቂቃ 43.9 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 43 ደቂቃ 22.9 ሴኮንድ ምስራቅ የተፃፈው ጉልት ስድስት ድረስ፣

ሰ. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ የአምራኩባ ተራራን ትይዩ በመከተል በአምራኩባ ተራራና በበርሚል ወንዝ

C. Thence, at the rim of Derahasen cliff Sholla Wuha, 12 degrees, 07 minutes, 45.5 seconds north and 35 degrees, 47 minutes, 28.3 seconds east (up to Post No. 3);

D. Thence, turning to north easterly direction, following the Derahasen Mountain cliff, up to the end of Gelego Kebele, extending to Alwasho Mountain and following the Alwasho valley that starts at Mehadid Kebele under the Alwasho Mountain, at the junction of the valley and Alatish dry weather road, 12 degrees, 15 minutes, 07.3 seconds north and 35 degrees, 44 minutes, 16.5 seconds east (Post No. 4);

E. Thence, following the valley and at its junction with the Bermil River, 12 degrees, 16 minutes 10.9 seconds north and 35 degrees, 43 minutes, 16.2 seconds east (up to Post No. 5);

F. Thence, to the northerly direction, following the Bermil River, parallel to the Amrakuba Mountain at the bank of the river, 12 degrees, 18 minutes, 43.9 seconds north and 35 degrees, 43 minutes, 22.9 seconds (up to Post No, 6);

G. Thence, in the same direction, following the opposite of the Amrakumba Mountain between the mountain and the Bermil

www.abyssinialaw.com



መካከል በ12 ዲግሪ 21 ደቂቃ 45.1 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 2 ደቂቃ 39.3 ሴኮንድ ምስራቅ የተጻፈው ጉልት ሰባት ድረስ፣

ሸ. ቀጥሎም በዚያው አቅጣጫ በአምራኩባ ተራራ ትይዩ ዲናር ወንዝ ዳር ላይ በ12 ዲግሪ 22 ደቂቃ 33.4 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 42 ደቂቃ 43.6 ሴኮንድ ምስራቅ የተፃፈው ጉልት ስምንት ድረስ፣

ቀ. ከዚያም የአምራኩባ ተራራን ወደ ፓርኩ ክልል በማስገባት ከተራራው ግርጌ በ12 ዲግሪ 23 ደቂቃ 53.3 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 43 ደቂቃ 7.7 ሴኮንድ ምስራቅ እስከተፃፈው ጉልት ዘጠኝ ድረስ፣

በ. ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ፡-

- ➔ ጉልት አስር በ12 ዲግሪ 24 ደቂቃ 46.6 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 41 ደቂቃ 28.7 ሴኮንድ ምስራቅ ላይ፣
- ➔ ጉልት አስራ አንድ በ12 ዲግሪ 24 ደቂቃ 46.5 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 41 ደቂቃ 10.8 ሴኮንድ ምስራቅ ላይ፣
- ➔ ጉልት አስራ ሁለት በ12 ዲግሪ 25 ደቂቃ 9.5 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 40 ደቂቃ 54.7 ሴኮንድ ምስራቅ ላይ፣
- ➔ ጉልት አስራ ሦስት በ12 ዲግሪ 24 ደቂቃ 54.3 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 40 ደቂቃ 30.7 ሴኮንድ ምስራቅ ላይ
- ➔ ጉልት አስራ አራት በ12 ዲግሪ 25

River, 12 degrees, 21 minutes, 45.1 seconds north and 35 degrees 2 minutes, 39.3 seconds east (up to Post No. 7);

H. Thence, in the same direction, in front of the Amrakuba Mountain at the bank of Dinar River, 12 degrees, 22 minutes, 33.4 seconds north and 35 degrees, 42 minutes, 43.6 seconds east (up to post No. 8);

I. Thence, making the Mukraba Mountain part of the park, at the foot of the mountain, 12 degrees, 23 minutes, 53.3 seconds north and 35 degrees, 43 minutes 7.7 seconds east (up to Post No. 9);

J. Thence, turning to north-westerly direction:

- ➔ (Post No. 10), 12 degrees, 24 minutes, 46.6 seconds north and 35 degree, 41 minutes 28.7 seconds east;
- ➔ (Post No. 11), 12 degrees, 24 minutes, 46.5 seconds north and 35 degrees, 41 minutes, 10.8 seconds east;
- ➔ (Post No. 12), 12 degrees, 25 minutes, 9.5 seconds north and 35 degrees, 40 minutes, 54.7 seconds east;
- ➔ (Post No. 13), 12 degrees, 24 minutes, 54.3 seconds north and 35 degrees, 40 minutes, 30.7 seconds east;
- ➔ (Post No. 14), 12 degrees, 25 minutes,

www.abyssinialaw.com



ደቂቃ 10.1 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 39 ደቂቃ 52.4 ሴኮንድ ምስራቅ ላይ፣

➔ ጉልት አስራ አምስት በ12 ዲግሪ 25 ደቂቃ 24.6 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 37 ደቂቃ 43.3 ሴኮንድ ምስራቅ ላይ፣

➔ ጉልት አስራ ስድስት በ12 ዲግሪ 26 ደቂቃ 03.8 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 38 ደቂቃ 47.4 ሴኮንድ ምስራቅ ላይ፣

➔ ጉልት አስራ ሰባት በ12 ዲግሪ 27 ደቂቃ 07.4 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 38 ደቂቃ 19.0 ሴኮንድ ምስራቅ ላይ፣

➔ ጉልት አስራ ስምንት በ12 ዲግሪ 27 ደቂቃ 50 ሰኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 37 ደቂቃ 48.9 ሴኮንድ ምስራቅ ላይ፣

➔ ጉልት አስራ ዘጠኝ በ12 ዲግሪ 28 ደቂቃ 47.5 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 37 ደቂቃ 17.5 ሴኮንድ ምስራቅ ላይ፣

የተጻፉትን ጉልቶች ተከትሎ ይሄድና ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ገለጎ ወንዝ ጥግ ልዩ ስሙ አምጃሌ ከተባለው ቦታ ላይ በ12 ዲግሪ 30 ደቂቃ 27.2 ሴኮንድ ሰሜንና በ35 ዲግሪ 37 ደቂቃ 14.1 ሴኮንድ ምስራቅ እስከተጻፈው ጉልት ሃያ ድረስ፣

ተ.ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍና የገለጎ ወንዝን ድንበር በማድረግ እስከ ኢትዮጵያና ሱዳን ዓለማቀፋዊ ድንበር ድረስ፣

ቸ. ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ

10.1 seconds north and 35 degrees, 39 minutes, 52.4 seconds east;

➔ (Post No. 15), 12 degrees, 25 minutes, 24.6 seconds north and 35 degrees, 37 minutes, 43.3 seconds east;

➔ (Post No. 16), 12 degrees, 26 minutes, 03.8 seconds north and 35 degrees, 38 minutes, 47.4 seconds east;

➔ (Post No. 17), 12 degrees, 27 minutes, 07.4 seconds north and 35 degrees, 38 minutes, 19.0 seconds east;

➔ (Post No. 18), 12 degrees, 27 minutes, 50 seconds north and 35 degrees, 37 minutes, 48.9 seconds east;

➔ (Post No. 19), 12 degrees, 28 minutes, 47.5 seconds north and 35 degrees, 37 minutes, 17.5 seconds east;

Following these posts and turning to the northern direction near the Gelego River at a place named Amjalie, 12 degrees, 30 minutes, 27.2 seconds north and 35 degrees, 37 minutes, 14.1 seconds east up to (Post No. 20);

K. Thence, turning to westerly direction, and taking the edge of the Gelego River, up to the international Ethio-Sudanese border;

L. Thence, turning to southerly direction, and

www.abyssinialaw.com



በመታጠፍ በምዕራብ በኩል የኢትዮጵያና ሱዳን ዓለማቀፋዊ ወሰንን ተከትሎ የአይማ /ዲንደር/ ወንዝ ከኢትዮጵያ እስከሚወጣበት ቦታ ድረስ፣

ኀ. ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ በደቡብ በኩል የአማራንና የቤንሻንጉል ጉሙዝን ብሔራዊ ክልሎች የሚያዋስነውን የአይማ /ዲንደር/ ወንዝ ተከትሎ በመሄድ እስከ አይማና አልቢድ ወንዞች መገናኛ ድረስ፣

ነ. ከዚያም የአልቢድ ወንዝን ተከትሎ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ወንዙን ተከትሎ ይሄድና አልቢድ ኮረብታ ጥግ ከወንዙ ዳርቻ ላይ ተጽፎ እስከሚገኘው መነሻ ጉልት ቁጥር አንድ ድረስ ይደርሳል።

## 4. ዓላማ

የፓርኩ ክለላ ዋና ዓላማ በሰሜናዊ ምዕራብ አካባቢ የሚገኘውን ወካይ ቆላማ ሥርዓተ ምህዳርና በውስጡ የያዛቸውን የብዝሀ-ሕይወት ሀብቶች በነዋሪው ሕዝብ ቀጥተኛ ተሣትፎ ከጥፋት በመታደግና በመንከባከብ ለመጪው ትውልድ በቅርስነት የሚተላለፍበትን ብሎም በዘላቂነት ለአካባቢው ሕብረተሰብና ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው እድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ የሚያበረክትበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው።

## 5. ስለፓርኩ አስተዳደር፣ ተጠሪነትና ውስጣዊ አደረጃጀት

1. በአዋጅ ቁጥር 96/1996 ዓ.ም አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ፓርኩን

then moving west wards, following the international Ethio-Sudanese border up to the place where Ayma (Dinder) River leaves Ethiopia.

M. Thence, turning to the easterly direction and moving south wards following the Ayma (Dinder) River which borders the Amhara and Benishangul Gumuz National Regional States up to the common junction of Ayma and Albid Rivers;

N. Thence, turning to northerly direction, following the Albid River, it goes up to the initial post No. 1, turning at the bank of the river nearby the Albid hill.

## 4. Objective

The main objective of delimiting the park is to protect from danger and conserve the representative lowland ecosystem found in the north-western area of the Region with the bio-diversity resources it possesses through direct participation of the local inhabitants and to create a favorable condition in which it is to be passed down to the coming generation as a heritage as well as provide an appropriate contribution to the surrounding community and the overall economic development in a sustainable way.

## 5. Administration, Accountability and Internal Organization of the Park

1. The Regional Parks Development and Protection Authority shall, in accordance with the powers vested in it under the provisions of

www.abyssinialaw.com



የሚያስተዳድረው የክልሉ ፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ሲሆን ተጠሪነቱም ለዚሁ አካል ይሆናል።

2. ባለስልጣኑ ለፓርኩ ልማትና ጥበቃ አመች ሆኖ በሚያገኘው የፓርኩ አካባቢ ጽ/ቤቱን ያደራጃል፣ የሥራ አመራሩን ይሰይማል፣ እንደ አስፈላጊነቱ የጥበቃ ሃይሎችን ያሰማራል።
3. የክልሉ መንግስት ፓርኩን ለማስተዳደርና ለማልማት አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ ልማት አውታሮች ደረጃ በደረጃ እንዲዘረጉ ያደርጋል።

## 6. የፓርኩ ጽ/ቤት ተግባራና ኃላፊነት

የፓርኩ ጽ/ቤት በዚህ ደንብ መሠረት የተመለከቱት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

1. የፓርኩን ማኔጅመንት፣ ጥበቃና ልማት ሥራዎች በአስፈፃሚነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. ከአካባቢው የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር አካላት ጋር በመቀናጀት የአካባቢው ነዋሪ ሕብረተሰብ ፓርኩን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዲያዳብር ያስተምራል፣ ይቀሰቅሣል፣ ያደራጃል፣ ያስተባብራል።
3. ከአካባቢው አስተዳደር የፖሊስና የፍትህ አካላት ጋር በመተባበር በፓርኩ ውስጥ የተከለከሉ ተግባራትን በሚፈጽሙ ግለሰቦች ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።
4. የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጐብኚዎች ጉብኝት በሚያደርጉበት ወቅት ሊከተሉት የሚገባቸውን ደንብና መመሪያ በተለያዩ ዘዴዎች አስቀድመው እንዲያውቁ ያደረጋል።

Art. 7, sub. Art. 1 of the proclamation No. 96/2003, administer the park, with the latter's accountability being to the said organ.

2. The Authority shall organize the office in an area of the park it finds suitable for the development and protection, designate its management and assign guards, as may be necessary;
3. The Regional State shall, step by step, cause the development of infrastructures that are necessary for the administration and promotion of the park.

## 6. Duties and Responsibilities of the Park's Office

The office of the park shall, pursuant to this regulation, have the following duties and responsibilities:

1. Direct and supervise over the management, protection and development activities of the park in an executive capacity;
2. Educate, agitate, organize and co-ordinate the local community in conjunction with the pertinent woreda and kebele administrations so that it may develop the responsibility to protect the park;
3. In collaboration with the police and justice bodies of the local administration, cause the taking of legal measures against those individuals who commit prohibited acts in the park;
4. Cause the domestic and foreign visitors be pre-informed, through various methods, of the rules and regulations they have to observe, at times of visit;

www.abyssinialaw.com



5. ከሚሰጠው አገልግሎት የሚመነጩ ልዩ ልዩ ገቢዎችን በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል።

## 7. ስለተከተለከሉ ተግባራት

በፓርኩ ውስጥ ሊከናወኑ እንደሚችሉ ከተፈቀዱት ተግባራትና ከሚመለከታቸው አካላትም ሆነ ተሣታፊዎች ውጪ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም በዚህ ደንብ የተከለከለ ነው፡-

1. ማናቸውንም የጦር መሣሪያዎች በመግቢያ በር ላይ ለዘብ ሳያስረክቡ ይዞ መግባት፣
2. ሁከት መፍጠር ወይም ባለ ድምፅ መሣሪያዎችን ከመጠን አሣልፎ መጠቀም፣
3. የዱር እንስሳትን ማደን፣ ማስፈራራት ወይም ማስበርገግ፣
4. ዕፅዋትን መቁረጥ፣
5. የአዕዋፍና የተሣቢ እንስሳትን እንቁላል መውሰድ፣
6. ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ ቁሦችን ማንሳት፣ መውሰድ ማጉሳቆል ወይም ማበላሸት፣
7. የግብርና ሥራ ወይም የሕዝብ ትራንስፖርት መንገድ ግንባታ ማካሄድ፣
8. የቤት እንስሳትን ለግጦሽ ማሰማራት ወይም እነርሱን አስከትሎ በፓርኩ ውስጥ መንቀሳቀስ፣
9. የማዕድን ፍለጋ ወይም የቁፋሮ ስራ ማካሄድ፣
10. ለቱሪስቶች ማረፊያ እንዲሆኑ ተለይተው ከተወሰኑት ስፍራዎች ውጪ እሣት ማንደድ፣
11. መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ይዞ መገኘት፣
12. ማናቸውንም አይነት የእቃ ሽያጭና

5. Collect a variety of revenues arising from the service it provides using legal receipts.

## 7. Prohibited Activities

It is forbidden by this regulation to commit the following activities in the park, with the exception of those permitted to be practiced and the concerned bodies as well as participants thereof:

1. Entering the park with any firearms, instead of temporarily handing same over to the guards at the entrance point;
2. Creating nuisance or using sound instruments beyond limit;
3. Hunting for, frightening or driving away wild animals;
4. Cutting off plants;
5. Taking away eggs of birds and reptiles;
6. Picking up, taking away, damaging, polluting or ruining natural or man-made items;
7. Undertaking agricultural works or construction of roads for the use of public transport;
8. Letting domestic animals in the park for grazing or moving about therein with them;
9. Undertaking mineral exploration or mining activities
10. Making fire, with the exception of those places specifically reserved for the purpose of tourist lodges;
11. Moving about with the possession of poisonous substances;
12. Undertaking any types of sale or exchange of goods;

www.abyssinialaw.com



ልውውጥ ማካሄድ፣

13. ጐብኝዎች ለምግብ መያዣና ለመሳሰሉት የተጠቀሙባቸውን ሰው ሰራሽ ቁሶች በዘፈቀደ መጣል፣
14. በፓርኩ ክልል የመኖሪያ ቤት መስራት፣ ወፍጮ መትከል ወይም ሌሎች መሰል ተቋማትን መገንባት፣
15. በህግ ከተወሰነው ፍጥነት ውጪ ተሽከርካሪ መንዳት ወይም ከጠዋቱ 12 ሰዓት በፊትና ከምሽቱ 12 ሰዓት በኋላ በፓርኩ ውስጥ ማሽከርከር፣
16. የእንስሳት ማጥመጃ መሣሪያ ይዞ ወይም አጥምዶ መገኘት፣
17. ጭስ አልባ ከሆነው የቱሪዝም እንዱስትሪ ውጭ ሌሎች የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን።

13. Arbitrary or careless disposal of man-made materials used by visitors for packing food and similar purposes;
14. Establishing dwelling houses, planting grinding mills or construction of other similar institutions in the park;
15. Driving motor vehicles beyond the legally-prescribed speed limit or so doing at all before 6:00 a.m. in the morning and after 6:00 p.m. in the evening;
16. being apprehended with a trap or setting same in order to attack wild animals;
17. Carrying out industrial activities other than the smoke-free tourism industry.

## 8. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ለዚህ ደንብ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት።

## 8. Duty to Co-operate

Any natural or Juridical person shall have the duty to co-operate in the implementation of this regulation.

## 9. ዝርዝር መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ባለስልጣኑ ለዚህ ደንብ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

## 9. Power to Issue Specific Directives

The Authority may issue specific directives necessary for the full implementation of this regulation.

## 10. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

## 10. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikree Hig Gazette of the Regional State.

ባህር ዳር
መስከረም 4 ቀን 1998 ዓ.ም
ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ርዕሰ መስተዳድር

Done at Bahir Dar
This 14th day of September, 2005
Yosef Reta
Head of the Amhara National
Regional Government

www.abyssinialaw.com